# ተጋደም ወይ ቅደም

(ዓለሙ አሎ)

ሌባ በጨለማ ቤት ይሰረስራል
ድንገት ከነቁበት የቀን ጅብ ይሆናል።
ካላማረህ በቀር በገዛ እጅህ መሞት
ሌባ ሲሰረስር ባትሪ አታብራበት።
ባትሪ ካበሩበት ሰርስሮ ሲገባ
ካልገደለ አይለቅም አደገኛ ሌባ።
አናትክን ተርትሮ ጥርስህን አራግፎ
አስታቅፎህ ይሄዳል አንጀትክን ዘርገፎ።
በተለይም ደግሞ ሬከርድ ካለበት
ሰላም አያገኝም ካልቆረጠ አንገት።
ፈሪ ያንኮራፋል የተኛ አስመስሎ
"ከነፍሴ አይብስም ብሬን ይውሰድ" ብሎ።
ምን አልባት ከነቃህ በድንገት በርግገህ
ለማስመሰል ሞክር አይተህ እንዳላየህ
ምንም እንዳልሰማህ ጆሮ እንደሌለህ
ተከናንበህ ተኛ ድምጽህን አጥፍተህ።
አንገትክን ካነቀህ "በሕግ አምላክ አትበል"
መተዳደሪያ ደንብ ሌባ ምኑም አይደል
ሳትቀደም ቅደም ወንድም አትጥመልመል።
ሌባ የሚደፍርህ ልብህን አይቶ ነው
እግሬ አውጪኝ ይላል በጥፊ ካጮልከው።
ሌባ ሰው በፍጹም አይሄድም ምንተፋ
ጭምብሉን ሳያደርግ ኮፍያ ሳይደፋ።
ምንጊዜም የሌባ ደመኛ ጠላቱ
የሚያወልቅበት ነው ጭምብሉን ከፊቱ።
ካልሆነ በስተቀር በራሱ እሚመካ
የሌባን ሰው ጭምብል ማንም ሰው አይነካ።
ከቶ አትዘናጋ ሞኝ አትሁን ወንድም
ባትሪ ካበሩበት ሌባ እንደው አይለቅም
እንደ ጸጉር ቅማል ከራስህ አይወርድም።
አንዴ ከጠመደህ መቼ ይለቅሀል
የሰፈሩን ዱራ ያሰማራብሃል።
እንዳትሆን ሰለባ የሌባ ተቀባይ
ጉድ እንዳያረግህ የጥቅም ተካፋይ
ከቤትህ አትውጣ ግራና ቀኝ ሳታይ።
ምንጊዜም የሌባ ሰለባ እሚሆነው
ፈራ ተባ የሚል የሚያቅማማ ሰው ነው።
ከሁለት ያጣ እንዳትሆን ከነብስም ካዱኛ
ሳትቀደም ቅደም አለዚያ ግን ተኛ።
ማጅራት መቺ መፍራት ባንተ አልተጀመረም
የተኛ ሰው መስለህ ዝም ብለህ ተጋደም
ባትሪ ካበራህ ግን አትበል ወለም ዘለም
ደመ ከልብ እንዳትሆን ሳትቀደም ቅደም።
እርምጃ ካልወሰድክ ከሱ ቀድመህ ቶሎ
ሌባ ያስይዝሃል "ሌባ ሌባ" ብሎ።
ጭምብሉን አውልቀህ--ፊቱ ላይ አብርተህ
አንተ ዝም ካልከው------እሱም ዝም ካለህ
ራስህ ሌባ ነህ።